# ይድረስ ለአንድነት ሃይሎች ሁሉ !!

## ለኢሕአግ ፌስቲቫል የኢህአግ አባላት ከነበሩ የተቸረ ስጦታ!!

ክፍል አንድ

***<u>ስለ ኢህአግ መሰራች ተሰፋየ ጌታቸው አሟሟት እውነታው</u>***



**«ድሮውንም ሻቢያ ለኢትዮጵያ አንድነት ለሚታገል ሃይል ይረዳል ብለን ማሰባችን ስህተት ነበር። »**

**ተስፋየ ጌታቸው**

**«የኢህአግን ትግል ማገዝ ለሚፈልጉ ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውናን የምናሳሰበው ነገር ቢኖር እርዳታቸው በትክክል በትግሉ ሜዳ ላይ ላሉት መድረሱን፤ የተረፋትን የኢሕአግ ታጋዮች በሻቢያና በቅጥረኞቹ ለማጥፋት አለመዋሉን የማረጋገጥ ሃላፊነት እንዳለባቸው ነው። »**

***ከትግል ጓዶቹ***

*<u>ለ መግቢያ ፦</u>* ይህን መልእክት የምናስተላልፈው ለአገርና ለወገን ብለን ኢህአግን ለመገንባት በተለያየ ሃላፊነት ላይ ታች ያልን የተሰፋየ የትግል ጓዱቹ የነበርን ግን ሳንወድ በግድ ከኢህአግ የተለየን ነን። ሀገራችንን ኢትዮጵያን ከገባችበት አዘቅት ለማውጣት የዜግነት ገዳጃችንን ለመወጣት ስንባዝን ነበር ኢህአግን በተለያየ ጊዜና ቦታ የተቀላቀልነው። የሻቢያ ሌት ተቀን ልፈፋ እውነት መስሎን የከፍተኛ ተቋማት ትምህርታችንን አቋርጠን ከአዲስ አበባ ጭምር ተጉዘን የተቀላቀልነው አለን። ኢሕአግ ከተሰፋየ ጌታቸውና ከሻቢያ ጋር አገናኘን። የትጥቅ ትግል ከወያኔ አገርን ማላቀቂያው ብቸኛው መንገድ ነው ብለን በማመን ረሃቡን፤ ጥማቱን፤ ቁርና ሀሩሩን ንቀን በህልፈታችን አገራችን ለመታደግ የቆረጥን ወጣቶች ነበር። የኢትዮጵያ አርበኞች ግንባር ከምሁር እስከ ገበሬ፤ ከአስተማሪ እስከ አስተማሪ፤ ከወጣት እስከ ሽማግሌ ከሁሉም ብሄር ብሄረሰብ የተውጣጡና ኢትዮጵያን ከወያኔ አረመኔዊ አገዛዝ ለማላቀቅ ቆርጠው የተነሱ የተሰባሰቡበት ነበር። ኤርትራ ውስጥ መሰረት ጥለን ወደ ዋናው የትግል ሜዳ ወደ አገራችን ለመግባት ደከመኝ ሰለቸን ሳንል ሌት ተቀን በወኔና በሞራል የትግል ቤታችንን ኢህአግን ለመገንባት እጅግ ጣርን። የሻቢያ አላማ አልገባንም ነበር። ሻቢያ የአንድነት ሃይሉን ከፋፍሎና አዳክሞ የጎሳ ድርጅቶችን አጠናክሮ አገሪቱ ወደማያባራ ትርምስ እንድትገባለት ብቻ መሆኑን የገባን እጅግ ዘግይቶ ነው። ሻቢያ እቅዱን ለማሳካት የግንባሩን አመራር ራሱ በሚያዛቸው ሰዎች ስር የማድረግ እቅዱን የተቃወሙትን ግማሾቹን ገደላቸው። ግማሾቹን ከትግሉ ውጭ አደረጋቸው። ከገደላቸው ውስጥ ተሰፋየ ጌታቸው አንዱ ነው። ከትግሉ ውጭ ካደረጋቸው ኮለኔል ታደሰ አንዱ ነው። በሻቢያና እንደ አበሩ አታላይና ሙሴ ተገኝ አይነት በሻቢያ አሽከሮች የታሰሩ፤ በቶርች የተሰቃዩና

አካላቸውን ያጡ የኢሕአግ አባላት አያሌዎች ናቸው። ይህን የምስክረነት ቃላችንን በይፋ ለመስጠት የፈልግነው ሌሎች እንደ ተስፋየ ጌታቸው ውድ ህወታቸውን ለአገራቸው አሳልፈው መስጠት የፈለጉ ውድ የአገሪቱ ልጆች የሻቢያን የተለያየ የማታለያና የማጭበርበሪያ ፐሮፓጋንዳ ሰምተው ሰለባ እንዳይሆኑ ነው። የደረሰብንና የምናውቀውን ለወገናችን ባናሳውቅ ለአገራቸው ሲሉ በማያቁት አገር በሻቢያና ሻቢያ እንዳሻው በሚያዛቸው አስመሳይ ታጋዮች ስቃይና መከራን ተቀብለው ያለፉትን ተስፋየ ጌታቸውንና ሌሎች አያሌ ውድ ጓዶቻችን አጥንት የሚረግመን መሰለን። እረፍት ነሳን። የዜግነት ግዴታም ሆኖ አገኘነው። ተስፋና ኮሌኔል ታደሰ የገነቡትን ኢሕአግን ለማፍረስ ብዙ የሰሩት ሙሤና መስከረም (ሌሎችም ሊኖሩ ይችላል) የኢሕአግ ፌስቲቫል በሚል ጀርመን ላይ ለማክበር መሰናዶ ላይ መሆናቸውን ስንሰማ እኛም ለፌሲቲቫሉ ይህችን ውድ ስጦታ ለማበርከት ለራሳችን ቃል ገባን። የሻቢያን የረቀቀ ተንኮል መረዳት ያስችላል በሚል ይህን ክፍል አንድ ስጦታችንን 1. ስለ ተስፋየ ጌታቸው ከምናውቀው በትንሹ 2. ኢህአግን ሻቢያ እንዴት እንዳዳከመው 3. ሻቢያ ኢህአግን አይን ባወጣ መልክ ሁለት ቦታ ለመከፋፈልና ለማዳከም ምክንያቱ 4. ወደ ተስፋየ ጌታቸው ሞት ያመራው ሁኔታ 5. የተስፋየ ጌታቸው መልእክት ! 6. ለተስፋየ ጌታቸው ሞት ተጠያቂው ማነው !7. የተስፋየና የኮለኔል ታደሰ ጦር ከአበሩ ጦር ጋር መቀላቀል 8. ሻቢያ በኢትዮጳያ ህዝብ አርበኞች ግንባር አባላት ላይ ከሚፈጽማቸው ወንጀሎች ጥቂቶቹን 9. የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ጦር አባላትና የሻቢያ የጉልበት ስራ 10. ኢህአግን በማፍረስ የዶክርተር ሙሴ ሚና 11. ስለ አበሩ አታላይ በትንሹ በሚል ከፋፍለናቸዋል። እንብበው እንዲያስራጩ ፈቃዳችንን ሰጥተናል። ሻቢያዎች እገር ለማፍረስ የሌለ ታሪክ ሲጽፉ ሻቢያ የሚፈጽመውን ወንጀል ለወገን ማድረስ መብት ብቻም ሳይሆን ግዴታም ነው።

ኢትዮጵያችን ከወያኔና ከሻቢያ መንታ ጠላቶች ነጻ እናወጣታለን!

ሚያዚያ 22 ቀን 1998 ዓ.ም.

ከተስፋየ የትግል ጓዶቹ

1. ስለ ተስፋየ ጌታቸው ከምናውቀው በትንሹ

ባለን ኢንፎርሜሽን መሰረት ተስፋየ ጌታቸው በ1983 እ.አ.ዩ የገባና በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የህግ ተማሪ የነበረ፤ በ1983ዓ.ም ወያኔን በመቃወምና የኢትዮጵያ ጦር ወያኔን እንዲቋቋም ሞራል ለመስጠት ወደ ብላቴ ወታደራዊ ማሰልጠኛ ከገቡት ወደ አስር ሺህ ከሚጠጉ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች አንዱ ነበር። በ1985 ዓ.ም የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችን የተቃውሞ ትግል የመራው የተማሪዎች ካውንስል አባልና በኋላም ወደ ኬንያ ከተሰደዱት የካውንስሉ አባላት አንዱ ነበር። ተስፋየ ለትጥቅ ትግል ከኬንያ ወደ ሱዳን ከሄዱት የኢህአፓ አባላት አንዱ የነበረና የኢትዮጵያ አንድነት ግንባር ሰራዊት ውስጥ በፖለቲካ ካድሬነት ለሁለት አመታት አገልግሏል። የኢአግ ወታደራዊ እንቅስቃሴ በውስጣዊና ውጫዊ ችግሮች በ1991 ዓ.ም መጀመሪያ ላይ ሲቆም ወደ ካርቱም ተሻግሮ የራሱን ድርጅት በማቋቋም የሻቢያን ጥሪ ተቀብሎ ወደ ኤርትራ በመሄድ የኢትየጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር እንዲመሰረት ከፍተኛ ጥረት ካደረጉት አንዱ ነው። ተስፋየ ደፋር፤ ላመነበት ወደ ኋላ የማይል፤ አንደበተ እርቱ ነው። የዚህን ታግሎ ያታጋለ ቀራጥ ኢትዮጵያዊ በሻቢያ እጅ ተሰቃይቶና ህክምና ተነፍጎት ህይወቱ እንዴት እንዳለፈ ወረድ ብለን በቦታው እንናብራራለን።

2. ኢ.ህ.አ.ግን ሻቢያ እንዴት እንዳዳከመው

የአርበኞች ግንባር የተመሰረተው ጥቅምት 1993 ዓ.ም. በተደረገ ጉባኤ ነው:: መስራች ድርጅቶችንም 1. የጋምቤላ ( በትዋት ፖል የሚመራ) 2. የቤኒሻንጉል 3. የከፋኝ (በአበሩ አታላይ/መስከረም እና ዮሴፍ) 4. ኢአዴን ( በተስፋየ ጌታቼውና በይኸነው የሚመራ) ድርጅቶች ናቸው። በጉባኤው ኮ/ል ታደሰ ሊ/መል ትዋት ፖል ም/ል ሊ/መ ሆነው ተመረጡ። ብዙም ሳይቆይ አመራር የተባሉትን ሻቢያ እርስበርስ ማናከስ ጀመረ። የጋንቤላው ትዋት ፓልና የቤኒሻንጉሉ ጁማ የብሄር አድሎ ይደረጋል። ለአማራና ለትግሬ የተለየ ጥቅምና ጠቅም ያለ ገንዘብ በስምሪት ወቅት ይሰጣል። አናሳ ብሄሮች ይጨቆናሉ ፤ የቀለም ልዩነት ይደረጋል ወዘተ በሚል ኮ/ል ታደሰን መክሰስ ይጀምራሉ። በሻቢያ ተንኮል ትንሽ ቆይተው ሁለቱም ድርጅቶቻቸውን ከግንባሩ ያስወጣሉ። አበሩ አታላይ/መስከረምም እንዲሁ በኮ/ል ታደስና በተስፋየ ጌታቸው ላይ ቅሬታ ማስማት ይጀምራል። በሻቢያ አቀነባባሪነትና ረዳትነት አበሩ/መስከርም በኮ/ል ታደስ ላይ ከፍተኛ የስም ማጥፋት ዘመቻ ይጀምራል። በዚህ መሃል የሰራዊት የስምሪት ሚስጥር በማባከን ተከሶ አበሩ አታላይ በ1994 ታስሮ ለሻቢያ ተሰጠ። ነሃሴ 1995 ሁለተኛው የግንባሩ ጉባኤ ተካሄደ። ጉባኤው የኢአዴን እና የመስከረም (ከፋኝ)ድርጅት እንዲሁም በግላቸው የተቀላቀሉ ታጋዮች የተገኙበት ነበር። በዚህ ጉባኤ ኮ/ል ታደሰ ሊቀመንበር ዮሴፍ ምክትል ሊቀመንበር ተስፋየ የፖለቲካ ሃላፊ ሆነው ተመረጡ። በዚህ ወቅት ድርጅቱ የተሻለ እንቅስቃሴ ያደረገበትና የሰፋበት ነበር።

3. ሻቢያ ኢህአግን አይን ባወጣ መልክ ለመከፋፈልና ማዳከም ምክንያቱ

የኢሕአግን መጠናከር ሻቢያ አልወደደም። ወደ ዝርዝር ሳንገባ በዋናነት ኢህአግ ከሻቢያ ቁጥጥር ውጭ የሚሆንበትን ዝግጅት  መጀመሩን ሻቢያ ማወቁ ነው። ኢሕ አግ ከሻቢያ ቁጥጥር እንዲወጣ ቁልፍ ሚና በመጫወት ላይ የነበረው ተስፋዬ ነበር። ይህ ሻቢያን በጣሙን ያበሳጫል። ሻቢያ «ይች ባቄላ ካደረች...» በሚል ስሌት ኢሕአግን ሊያጠፋ ተነሳ። ሻቢያ በይፋ ጣልቃ ለመግባት እንደሰበብ የተጠቀመው ግን የኢህአግ ስራ አስፈጻሚ አመራር የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ሃይሎች ህብረት አሜሪካ ላይ በተመሰረተ ወቅት ድጋፉን የሚገልጽ መግለጫ በተለይ በተስፋየ ጌታቸው ግፊት ጥቅምት ላይ ማውጣቱን ነው። ሻቢያ «እንዴት እኛን ሳታማክሩ እንዲህ አይነት መግለጫ ታወጣላችሁ» በሚል ይቆጣል።

በዚህም የተነሳ አመራሩ ችግር አለበት በሚል በህዳር ወር 1996 እንደገና አስቸኳይ ጉባኤ እንዲጠራ ሻቢያ ትእዛዝ ይሰጣል። አዲዮስ! የኢሕአግ ውስጣዊ ነጻነት ተገሰሰ። መስከረምን ከእስር ፈቶ ለምርጫ አዘጋጀው። የግንባሩ አመራር አራት ወር ባልሞላ ጊዜ እንዴት ይሆናል ቢልም ሰሚ የለም። ከጉባኤው ቀደም ብሎ በሻቢያ አቀነባባሪነት አበሩ በኮኔል ታደሰ ላይ አያሌ የሃሰት ክስና የስም ማጥፋት ዘመቻ አካሄደ ። ጉባኤው ተጀመረ ። በጉባኤው ላይ መስከርም በሻቢያ አቀናባባሪነት ያሰራጫቸው ወሬዎች በሙሉ ሃሰት ሁነው ተገኙ። ሻቢያ አበሩ አታላይን በሊቀ መንበርነት ለማስመረጥ ሲል  ሀ) ኮ/ል ታደሰን ለ) አበሩ አታላይን ሐ) ተስፋየ ጌታቸውን መ) ዮሴፍ የተባለን ሰው ለምርጫ እንዲወዳደሩ አዘዘ። ይህ ሁሉም ለስልጣን ይሮጣል በሚል እርስ በርስ አጠላልፎ በመሃል መስከረምን ለማስመረጥ ነበር ። ነገር ግን የሻቢያ ሴራ ታውቆ ስለነበር ተስፋየ ጌታቸው እድሜየና ተመክሮየ አይፈቅድም በሚል፤ ዮሴፍ በሽተኛ ነኝ አልችልም የሚል ምክንያት በመስጠት ኮ/ል ታደሰ ቢመረጥ የሚደግፉ መሆናቸውን በመግለጽ ራሳቸውን ከምርጫው አገለሉ። ሻቢያ መስከረምን/ አበሩን ለማስመረጥ  የጠሩ አባላትን በገንዘብ እስከመ ደለልም ደርሷል። የሆነ ሁኖ ሀ) ኮ/ል ታደሰ ከሶስት አራተኛ በላይ  ድምጽ በማግኘት ሊ/መ ሆኖ እንደገና ተመረጠ ለ) መስከረም ከአንድ ሶስተኛ ያነሰ ድምጽ በማግኘት የምክትል ሊቀመንበርነቱን ቦታ አገኘ። በጉባኤው የአመራር ምርጫ ውጤት ሻቢያ እጅግ በመበሳጨቱ  የዚያኑ እለት

1. አበሩ ደጋፊዎቹን ይዞ ከኮል ታደሰ ቡድን እንዲለይ አዘዘ ። ወደ ሰባ የሚጠጉ የወልቃይትና አርማጨሆ ተወላጅ የሰራዊት አባላት ተከተሉት። ለአበሩ ሰዎች የዚያኑ ቀን ልዩ ትጥቅ በሻቢያ ተሰጣቸው። ካምፕ ተቀየረላቸው።
2. ሻቢያ ኮ/ል ታደሰን፤ ተስፋየ ጌታቸውን እንዲሁም ዮሴፍን በመደገፍ የቆመው የሰራዊት አባል ከፍተኛ መሆኑ አሳሰበው በመሆኑ ከኮ/ል ታደሰ ጋር የቀሩትን ታጋዮች «ሁሉም በየብሄረሰቡ ተደራጅቶ  መታገል አለበት »በሚል ማጭበርበሪያ ኦሮሞዎችን ለኦነግ፤ ትግሬዎችን ዴሞክራሲያዊ ምንቅስቃስ ትግራይ ድርጅት ፤ የደቡብ ተወላጆችን ለሲዳማ አርነት ድርጅት

ያለውዴታቸው አሳልፎ ሰጠ። ሻቢያ ኮ/ል ታደሰና ተስፋየ አማራ የተባለውን ብቻ ይዘው እንዲቀሩ በጣም ጣረ። በዚህ አይነት ከ60 በላይ አባላት ለ ኦነግ፤ ለሲዳማ ነጻ አውጭ፤ ለትግራይ ዴሞክራሲያዊ እንቅስቃሴ፤ ወዘተ ያለውዴታቸው ሻቢያ ሰጥቷል። እምቢ ያሉትን አሰቃይቷል። (ለምሳሌ ስሙን መጥቀስ አስፈላጊ ያልሆነ ታጋይ እኔ በብሄረሰብ ነጻ አውጭ ድርጅት ስር አልታገልም በማለቱ በሻቢያ ታሰሮና ተገርፎ አካለ ስንኩል እስከመሆን ቢደርስም ከአላማው አልተበገረም።) ያም ሆኖ የጉራጌ፤ የአማራ፤ የኦሮሞ፤ የትግራይ፤ ወዘተ ብሄረሰብ ተወላጆች ከነተስፋየ ቡድን ወግነውና ሻቢያን አሳፍረው ቀርተዋል። የሲዳማ ነጻነት ግንባርና ዴምት የተጠናከሩት ከኢሕአግ በሄዱ ልጆች ነው። ልብ በሉ ለኢትዮጵያ አንድነት የሚታገለውን አፍርሶ የጎሳ ነጻ አውጭዎችን ማጠናከሩን።

3. ኮል ታደሰና ተስፋየ ጋር የቀረው ወደ 200 የሚጠጋ ሰው አብዛኛው ትጥቅ ፈቶና ጀሌ ሆኖ ራቅ ወዳለ ካምፕ ተወስዶ እንዲቀመጥ ተደረገ። ውሃና ህዝብ የሌለበት፤ አዲ ነፋስ ወደ ተባለ ቦታ ተላከ። የነተስፋየ ጦር የታጠቀው መሳሪያ አሮጌ፤ የዛገና አብዛኛው የማይተኩስ በጠቅላላው ከ40 የማይብልጥ ክላሽ ነበር።
4. እንደዛሬው ይፋ ሳይወጣ ሙሴ ተገኝ ከጀርባ ሆኖ የሚያዘው የአበሩ ቡድን ያልታጠቀው የነኮል ታደሰ ጦር ያለበት ቦታ ድርስ በመሄድ በመደለልም፤ በማስፈራትም፤ በጉልበትም ሰው መውሰድ የዘወትር ተግባር አደረገው። በአንድ ቀን ብቻ በሻቢያ ወታደሮች ድጋፍ 15 ሰዎችን አስገድደው ወሰዱ። ይህ ተስፋየን አበሳጭቶ « የሻቢያ ወታደረም ቢሆን ያለፈቃድ ካምፓችን ውስጥ ከመጣ እንዳትምሩት» ሲል ትእዛዝ እስከመስጠት ያደረሰውና ለሞቱ እንደሰበብ የሆነውን ሰላማዊ ስልፍ ለማቀድ ይበልጥ ገፋፋው።

ሻቢያ ድርጅቱ ከሁለት እንዲከፈል ካስደረገ በኋላ ሁኔታዎች ጭራሹኑ ተበላሹ ዘርንና ቋንቋን መሰረት ባደረገ መልኩ ለአንድ አላማ የተሰለፉ ታጋዮች በሁለት ጎራ ተከፋፍለው በክፉ አይን መተያየት እንዲጀምሩ አደረገ። ሻቢያ በአንድ ላይ ሊታገሉ የመጡትን ታጋዮች የመስከረም ደጋፊና የነተስፋየ ጌታቸው ደጋፊ በማለት ከፋፈላቸው። ለተስፋየና ለኮለኔል ታደሰ ደጋፊዎች መሰረታዊ የሆኑ ቁሳቁሶችን ሳይቀር መከልከል ያዙ። የህክምና፤የራሽን፤ የመሳሪያ፤ የይለፍ ፈቃድ ፤የአልባሳት እና ሌሎች ድጋፎችን እየሰጠ ለተስፋየና ለኮለኔል ታደሰ ቡድን ከለከለ። በዚህ የተበሳጩ አባላት ለግዳጅ እንደሄዱ መክዳት፤ እዚያው ያሉትን እየጠፉ ወደ ስደት ሄዱ፤ ለከፈተኛ መከራ ፤ ለእስርና እንግልት ተዳረጉ። አንድ ህክምና ወይም ሌላ አገልግሎት ፈላጊ በመጀመሪያ የሚጠየቀው የተስፋየ ወይም የአበሩ/መስከረም ደጋፊ መሆኑ ነው። የተስፋየ ነኝ ካለ ይዘለፋል፤ ይዋከባል፤ ሞራሉን ለመንካት ያጉላሉታል። አብዛኛውን ጊዜም ይከለክሉታል። የልብስ መጠቆሚያ መርፌ እንኳ እስከመከልከል የደረሱበት ሁኔታም ነበር። በተቃራኒ ግን የአበሩ/መስከረም ደጋፊ ነኝ ካለ በክብርና ያለምንም ውጣውረድ ቅድሚያ ተሰጥቶት ይስተናገዳል ። ህክምና ከሆነም እስከ ተሰነይ ድርስ ሄዶ እንዲታከም

ያደርጉታል። ይህ በአብዛኛው የሰራዊት አባላት ላይ ከፍተኛ ብስጭትና ተስፋ መቁረጥን እንዲሁም ሞራል መወደቅን አስከተለ።

4. ወደ ተስፋየ ጌታቸው ሞት ያመራው ሁኔታ

ተስፋየ ጌታቸው ሻቢያ ወክሎ ያስቀመጣቸው እንደን ኮሌኔል ፍጹምና ሻምበል ዳዊት አይነት ሹማምንት በኢትዮጵያውያን የውስጥ ጉዳይ ላይ ገብተው የሚፈጽሙትን በደል በግልጽ መቃወም ይጀምራል። ከዚያም አልፎ ለከፍተኛ የአገሪቱ ባለስጣናት አቤት ለማለት ከአዲነፋስ ከተባለው ካምፕ ማይሽግሊት የምትባለው ትንሽ ከተማ ድረስ ጦሩ ሰላማዊ ሰልፍ በማድረግ ብሶቱን እንዲያሰማ እቅድ ያወጣል። ሰላማዊ ሰልፉ ይደረጋል። የአካባቢው የሻቢያ ባለስጣናት ጥያቄውን ለበላይ እንደሚያቀርቡና በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ መልስ እንደሚመጣላቸው ነግረው ወደ መጡበት እንዲመለሱ ይሸኟቸዋል። ከወር በኋላ እንደተባለው ከአስማራ በጀነራል ተክሌ ማንጁስ የሚመራ ልኡክ መጣ። ከአስማራ የመጣው ቡድን የነተስፋየን ቡድን አመራር፤ የሻቢያ የአካባቢው ወኪሎችና የአበሩ ቡድን አመራሮችን በግራ ቀኝ አስቀምጦ የኢህአግን እንቅስቃሴ ከአዳመጠ በኋላ ለኢሕአግ መፍረስ ተጠያቂው ተስፋየ ጌታቸው ነው አለ። ተስፋየ ጌታቸው በበኩሉ እኔ ሳልሆን ተጠያዎቹ ሻቢያና መስከረም መሆናቸውን፤ ሻቢያ በኮልኔል ፍጹምና ሀድጉ አማካንነት እንዲሁም በሙሴ ተገኝ የሚታዘዘው መስከርም አማካይነት ኢሕአግ ሁለት ቦታ እንዲከፈልና እንዲዳከም መደረጉን አብራርቶ መልስ ሰጠ። በመጨረሻም በጀኔራል ተክሌ ማንጁስ የተመራው ቡድን ፍርድ ሀ) የኮሌኔል ታደሰ ጦር ከአዲ ነፋስ ወደ ሃሬና እንዲመለስ ለ) ተስፋየ ጌታቸው ህገወጥ ሰላማዊ ሰልፍ በማስተባበሩ ወንጀለኛ በመሆኑ እንዲታሰር ሲል በየነ። ተስፋየ ጌታቸው ከአምስት ቀን በኋላ ታሰረ። ኮሌኔል ታደሰን ጦሩ ሳያይና ሳይሰማ ተስፋየ በታሰረ በሶስተኛው ቀን ወደ አስማራ ተወሰደ። የኮሌኔል ታደሰና የተስፋየ ጦር ያለመሪ ቀረ። የቁም እስረኛ ሆነ። ተስፋ ጌታቸው እጅና እግሩ በሲባጎ ተጠፍሮ ታስሮ ተገረፈ፤ በኤሌክትሪክ ተጠበሰ። ተስፋየ አቅም አንሶት ራሱን ችሎ መጸዳዳት አቅቶት፤ የእግሩ መዳፍ ቆዳ ተግልፎ እንኳን መሬት ልብስ በማያስነካበት ደረጃ ላይ ደረሰ። ይህን ያዩ የሻቢያ ዘብ ጠባቂ ወታደሮች ሬሳ አንጠብቅም በሚል ለሁለት ተከፈሉ። ወይ ትእዛዝ ይሰጥና እንጨርሰው ያለ በለዚያ ከዚህ ውስዱ ህክምና ይሰጠው ሲሉ ቢያመለክቱም ሰሚ አላገኙም። በኋላ አንዱ የኩናማ ብሄረሰብ ተወላጅ የሻቢያ ጦር አባል እምቢ ያሉት የሻቢያ ወታደሮች ላይ መሳሪያ በማዞሩ አውጥተው ለይሰሙላ ወደ ህክምና ላኩት። ተስፋየ ግን ህይወቱ አትውጣ እንጂ አብቅቷል። እንደማይተርፍ ሲታወቅ ግንቦት 23 ቀን 1996 ከጠዋቱ አምስት ሰአት ለጓዶቹ አምጥተው አስረከቡት። ከቀኑ አስር ሰአት ላይ አረፈ። የዚያኑ እለት አሬና የተባለው የኢሕአግ አርበኞች የመቃብር ቦታ በትግል ጓዶቹ ሥርዓተ ቀብሩ ተፈጸመ።

5. የተሰፋየ ጌታቸው መልእክት !

ተሰፋዬ ጌታቸው ከማረፋና ከመድከሙ በፊት ለሚቀርቡት የኢህአግ አባላት የተናዘዘው « ድሮውንም ሻቢያ ለኢትዮጵያ አንድነት ለሚታገል ሃይል ይረዳል ብለን ማሰባችን ስህተት ነበር። አሁን እናንተ ከመስከርም ጦር ጋርም ቢሆን ተቀላቅላችሁ ሻቢያ ሳያጠፋችሁ ከዚህ አገር ጥፉ» የሚል ነበር። ተሰፋየ አያይዞም ሻቢያ አሰቃይቶ ሊገድለው ያሰበው ኢህአግን ኢትዮጵያን ለማፍረስ ሊጠቀምበት ማሰቡን አጥብቆ በመቃወሙ እንደሆነ በማስረዳት በፍጹም የሻቢያ መሳሪያ እንዳይሆኑ አስጠንቅቆ የሞትን ጽዋ በጸጋ ተቀብሏል። እንግዲህ ሻቢያ ተሰፋየን ለማጥፋት ለምን ፈለገ የሚል ጥያቄ ቢነሳ መልሱ አጭርና ግልጽ ነው። ተሰፋየ ሻቢያ የሚፍለገውን አምቢ በማለቱ፤ ከልቡ ኢትዮጵያዊ በመሆኑ፤ የግንባሩን አባላት በግንባሩ አላማ ዙሪያ ሊቀርጽ የሚችል ጽኑ አላማ ያለው በመሆኑ ነው።

6. ለተሰፋየ ጌታቸው ሞት ተጠያቂው ማነው !

ተሰፋየ ባጋጣሚ አመራር በመሆኑ ተነሳ እንጅ በመቶዎች የሚቆጠሩ የሱ እጣ የደረሳቸው አሉ። ተጠያቂው ተሰፋና መሰሎቹን ለምኖ ለደህንነታቸው ዋስትና እሰጣለሁ ብሎ የወሰዳቸው የሻቢያ መንግስት ነው። አበሩ አታላይና ሙሴ የሻቢያ ጉዳይ አስፈጻሚ ናቸው። ኮለኔል ታደሰ ተሰፋየ ጌታቸውን አሰሮት ነበር የሚለው የሻቢያና የቅጥረኞቹ የሙሴና የአበሩ ፈጠራ ነው። በእርግጥ ተሰፋየ ጌታቸው ታስሮ ነበር። እሱም እንዲህ ነው። የታሰረው አንድ የሻቢያ ካድሬ ለማህቶት ወይም ለማሽላ ቆረጣ (ጉልበት ስራ) 100 ሰው ስጠኝ ብሎት ባለመስማማቱ ነው። ተሰፋየ ያለው ሰው ለስምሪት ሊሄድ ዝግጅት ላይ ስለሆነ 50 ሰው ብቻ ነው ለጉልበት ስራው ያለኝ ይላል። የሻቢያው ካድሬ ቃሌ እንዴት አይከበርም በሚል በወቅቱ በአካባቢው የነበሩትን የግንባሩን አመራር አባላት ተሰፋየ ጌታቸውንና ይኸነው እንዲታሰሩ ትእዛዝ ይሰጣል። ተሰፋየ ቀድም አድርጎ ይኸነው በፕሮግራማቸው መሰረተ ጦር ይዞ ለስምሪት በቶሎ እንዲሄድ ያደርጋል። ይኸነው ከስር አመለጠ። ተሰፋየ ካምፕ ቁጭ ብሎ ሻቢያ የሚያደርገውን ጠበቀ። ታሰረ። ተሰፋየ የተፈታው ባደረበት ከፍተኛ ህመም የተነሳ ሞት አፋፍ ላይ ሲደርስ ነው። ተሰፋየ ሲታሰር ኮሌኔል ታደሰ በአካባቢው አልነበርም። የተሰፋየን በሻቢያ መታሰር ጠሩ እንዳያውቅና በተለይም በሁለቱ መሃል ቅራኔ ለመፍጠር ተሰፋየን ያሰረው ኮ/ል ታደሰ ነው ብሎ ሻቢያ አስወርቶ ነበር። ይህ ልክ አለመሆኑን ኮሌኔል ታደሰ ተሰፋየ ባለበት ለጠሩ አስረድቷል። ባጭሩ ለተሰፋየ ሞት ዋናው ተጠያቂ ሻቢያ ነው። ከላይ እንደተጠቀሰው እንዲታሰር ከፈረደው ከጀኔራል ተክሌ ማንጁስ በተጨማሪ በግርፋት ካሰቃዩት ውስጥ ሻምበል ዳዊት፤ ህድጎ፤ እና ወዲ ሀጎስ የተባሉ የሻቢያ ካድሬዎችም ይገኙበታል።

7. የተስፋየና የኮለኔል ታደሰ ጦር ከአበሩ ጦር ጋር መቀላቀልና የአበሩ በሻቢያ ትእዛዝ ሊ/መ መሆን

ኮለኔል ታደሰን ከጦሩ ለይተው ወደ አስማራ ከወሰዱት ከወር በኋላና ተስፋየ ባረፈ ባራተኛው ቀን ከኮለኔል ታደሰ የመጣ መልእክት ተብሎ ሀድጎ በሚባል የሻቢያ ካድሬ ለሰራዊቱ ተነበበ። የመልእክቱ ይዘትም « በአቅም ማጣት፤ በእድሜየ መግፋት፤ በጤናና በመሳሰሉት ችግሮች የተነሳ ድርጅቱን መምራት ስለማልችል ከዛሬ ጀምሮ የድርጅቱን አመራር ለመስከርም አስረክቤለሁ። ከመስከረም አታላይ ጋር አብራችሁና ተባብራችሁ ታገሉ» የሚል ነው። በጎን በሚስጥር ኮል ታደሰ ሲጠየቅ ግን ከአስማራ መውጫ አልሰጠኝ ብለው ነው እንጂ ለመምጣት እየጣርሁ ነው የሚል መልስ ተገኘ። ይህ የሻቢያ ድራማ መሆኑ ቢገባውም ምርጫ አልነበረም። በዚሁ መሰረት የኮል ታደሰን ሰዎች ግንቦት 27 ቀን እ.አ.አ 1996 ከመስከርም ሰዎች ጋር ወስዶ ቀላቀላቸው። ግንቦት 29 ቀን 1996 ሻቢያ አዲስ አወቃቀር ብሎ አወጀ። በዚህ መሰረትም አበሩ አታላይ/መስከረም አታላይ የድርጅቱ ሊ/መንበር መሆኑን ታወጀ። ድርጅቱ እስከሚጠናከርም ለያንዳንዱ የስልጣን ሃላፊነት በምክትልነት የሻቢያ ካድሬዎች ተሾሙ። ለአብነት ያህልም በ1997 የግንባሩ ም/ል ሊ/መ ሰለሞን፤ የዘመቻው ም/ል ሊ/መ ተስፋ፤ ሁነው የተሾሙት ሻቢያዎች ናችው። ሻቢያ ሙሉ ለሙሉ ድርጅቱን ተቆጣጠረው። ይህን አዲስ አወቃቀር በመቃውም ከዚያን ጊዜ ጀምሮም ሁሉም ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ በሰፋት መክዳት ተጀመረ። የኮል ታደሰና የተስፋየ ጽኑ ደጋፊዎች ናቸው የተባሉ ተለቅመው ታሰሩ። በሻቢያና በሙሴ ትእዛዝ ሰጪነት አበሩ ፊደል የቆጠሩትን፤ አላማ ያላቸውን፤ ነቃ ያሉትን፤ ሃገራዊ ራእይ ያላቸውን ባጭሩ ግንባሩ አሉኝ የሚላቸውን የኮለኔልና የተስፋየ ደጋፊ ሆኑም አልሆኑ ሻቢያ የሚያዘውን ሊቃወሙ ይችላሉ ብሎ ያሰባቸውን ከላፊነት ቦታ አነሳቸው። ወታደራዊ አመራሩን ሙሉ ለሙሉ የአበሩ ደጋፊ ለሆኑት ብዙም ከሽፍተነት ስነልቦና ላልተላቀቁት ለአርማጨሆና ለወልቃይት ተወላጆች ተሰጠ። የመሀል አገር ልጆችን ሰበብ ፈልጎ በማሰርና ከፍተኛ የጉልበት ስራ በማስራት ሞራላቸውን መንካት ተያያዘው። ሊያስራቸውና ሊገላቸው ያልፈጋቸውን ሻቢያ ወደ ኢትዮጵያ ገብታችሁ የመረጃ ስራ ስሩ በሚል መሸኘት ያዘ። (በነገራችን ላይ መረጃው ለሻቢያ እንጂ ለድርጅቱ አይደለም። መረጃ ለመሰብሰብ ወደ ኢትዮጵያ የሚላኩት ኢትዮጵያ ሁነው መረጃቸውን የሚያቀብሉት ለሻቢያ ካድሬዎች ነው። ሲመለሱም መጀመሪያ የሚቀበላቸው ሻቢያ ነው።) መጀመሪያ የግንባሩ ድጋፍ ሰጪ በሚል ስም በሻቢያ አማካይነት ግንባሩን የቀረበውና አላማው የተሳካለት ዶክተር ሙሴ ኮሌኔል ታደሰን የሚደግፉትን « እናንተ አንገቷን ተቀንጥሳ ተጥላ እንደምትንደፋደፍ ዶሮ ናችሁ የናንተ ነገር አብቅቷል።ኢሕአግ አንገቱ ተቆርጧል። »ሲል ተዘባብቷል።

8. ሻቢያ በኢትዮጳያ ህዝብ አርበኞች ግንባር አባላት ላይ ከሚፈጽማቸው ወንጀሎች

የተሻለ ግንዛቤ ያላቸውና የሻቢያን ጣልቃ ገበነት የሚቃወሙትን በጣም ጥቃቅን ስህተት ፈልጎ ያስራል። ሲያስራቸው ደግሞ ለግዜዊ ቅጣት ሳሆን አንድም ለመግደል አለያም በቀላሉ የማይድን አካላዊ ጉዳት እንዲደርስባቸው ነው። በመሆኑም ሲያስራቸው በካቴናና በሲባጎ ስርስሮ እጅና እግራቸውን ያስራቸዋል ከፍተኛ ድብደባ ይፈጽምባቸዋል። ስስ ብልታቸው ላይ ጉዳይት ያደርስባቸዋል። በዚም የተነሳ ሽንታቸውን መቋጠር የማይችሉ፤ ብልታቸው የማይሰራ፤ እጅና እግራቸው ሽባ የሆኑ እጅና እግራቸው የሰለሉ፤ ሌላም ፤ሌላም የአካል ጉዳት የደረሰባቸው እጅግ ብዙ ናቸው። ከላይ የተጠቀሰው አይነት ጉዳት የደረሰባቸውን ሁለት መኪና ሙሉ ሰዎች ታህሳስ 1997 ሱዳን ድንበር ላይ ሻቢያ ወስዶ አራግፏቸዋል። ከነዚህ በተጨማሪም ሻቢያ የአርበኞች ግንባር አባላትን በሃይማኖት፤ በአገር ልጅነትና በዘር በመከፋፍል በማናናቅ፤ የአናሳ ብሄረሰብ አሁንም በአማርው እየተጨቆነው የሚል ከፍተኛ ቅስቀሳ ያደርጋል። ያስደርጋል።

## 9. የሻቢያን ኢኮኖሚ ለመገንባት የጉልበት ስራ

ኤርትራ ውስጥ ያሉ የተቃዋሚ ድርጅት አባላት በበጋው በሳምንት ከሶስት ቀን ያላነሰ በተለይ በክረምት መደበኛ የጉልበት ስራ አገልግሎት ለሻቢያ ይሰጣሉ። ማህቶት ይሉታል። ሻቢያ የሽክላ ስራ፤ የግብርና ስራ፤ የመስኖ ልማት፤ ሌላም ሌላም ስራ ያሰራል። በተለይ በክረምት ሳምንቱን ሙሉ የጉልበት ስራ ነው። ይህን የጉልበት ስራ የተቃወመ፤ ይለግማል ተብሎ የተጠረጠረ፤ ጥያቄ ያነሳ አይቀጡ ቅጣት ይቀጣል። ይታሰራል ፤ ይገረፋል፤ ይደበደባል። የተሰጠው ስራ በተባለው ቀን ካላለቀ ስራው እስከሚያልቅ በየቀኑ ይቀጥላል። ሻቢያ የተቃዋሚ ጦር አባላት ለስምሪት ሄዱ አልሄዱ ግድ የለውም የተጠየቀው ኮታ መሟላት አለበት። ኮ/ል ታደሰና ተሰፋየ ጌታቸውን ከሻቢያ ጋር ካጣላቸው አንዱ ይህ ነው። በሰበብ አስባቡ የሚታሰሩ ደግሞ በቋሚነት ለሻቢያ የጉልበት ስራ ይሰራሉ።

## 10. ኢህአግን በማፍረስ የዶክርተር ሙሴ ሚና

ዶር ሙሴ ግንባሩን የቀረበው ኮምፒውተርና ሌሎችም መርጃ ቁሳቁሶችን በመርዳት ነው። ለአገው/ጎጃም ህዝብ መገንጠል የሚታገል ፈለገ ጊዮን /ሞገድ የሚባል ድርጅት አለኝ በሚል የግንባሩ አባል ለመሆን ቢሞክረም በድርጅቱ ስም ሰው ማምጣት አልቻለም። አንድ ተከታይ እንኳ በስሙ ማፍራት ያልቻለ ነው። ዶክተር ሙሴ ከሻቢያ ጋር ከ25 አመታት በላይ የዘለቀ ግንኙነት እንዳለው እሱም ሻቢያም አይሸሽጉትም ። ዶ/ር ሙሴ የሚታወቀው የኋላ ደጀን ወይም የግንባሩ ደጋፊ በመባል ነበር። ከአበሩ አታላይ ጋር እጅግ የጠበቀ ግንኙነት አለው። ሻቢያ አበሩን የግንባሩ ሊቀመንበር አድርጎ ለማስመረጥ ከፍተኛ ጥረት ያደረገው ዶ/ር ሙሴ ግንባሩን በአበሩ አማካይነት በእጅ አዙር እንዲቆጣጠርለት ነበር። ሙሴ ሻቢያ ለኮለኮላቸው ነጻ አውጪዎች ማለትም ኦነግ፤ የኦጋዴን ነጻ አውጭ፤ የትግራይ ዴሞክራሲያዊ እንቅስቃሴ፤ የጋንቤላ ነጻ አውጭ፤ የሲዳማ ነጻ አርነት ንቅናቄ፤ የቤኒሻንጉል ነጻ አውጭ ድርጅት ወዘተ በሙሉ ነጻ የሚያወጡትን ቦታ ካርታ

አውጥቶና በመጽሃፍ መልክ ጠርዞ በነጻ በማደሉ በሻቢያ ፕሮፌሰር የሚል ማእረግ ያገኘ ነው። የሙሴ ነገረ ስራ ሁሉ ከሻቢያ በተጨማሪ ምናልባትም ለሌላ ኢትዮጵያን ለማፍረስ ለተሰለፈ የውጭ ሃይል የሚሰራ ነው የሚመስለው። ሙሴ እያንዳንዱን የጠሩን እንቅስቃሴ በቪዶና በካሜራ አስቀርጿል። በቅርቡ ደግሞ የግንባሩ ድረ ገጽ አስተዳዳሪ አድርጎ ራሱን /በሻቢያ ተሰይሟል። በየትም ታይቶ በማይታወቅ መልክ የሽምቅ ተዋጊ አባላትን ፎቶ ለህዝብ ይፋ በማድረግ ንግዱን አጧጡፏል።

---

11. ስለ አበሩ አታላይ በትንሹ፦

አበሩ ወደ ኤርትራ የሄደው ከሱዳን ነው። አሁን እንደምንሰማው አበሩ ካርቱም እያለ በሲቲ ባንክ በኩል ለአበራ አታላይ የተላከ ገንዘብን የኔ ነው ብሎ አጭበርብሮ የወሰደ ግለሰብ ነው። አበሩ የዶክተር ሙሴ አምላኪ ነው። ሻቢያ አበሩን በስልጣን እንዲቀመጥ የሚፈልገው የሚታዘዘውን የሚፈጽም እንጅ ለምን ብሎ ለመጠየቅ ህሞቱም ሆነ ድፍረቱ እንዱሁም የአስተሳሰብ አድማሱ የማይፈቀድለት በመሆኑ ነው። አበሩ የወልቃይት ህዝብ ከኤርትራ የፈለሰ ነው የሚል ፈጠራን እውነት ብሎ የሚያስተጋባ ነው። አበሩ የግንባሩ ሃላፊ ከሆነ በኋላ ደግሞ በሙስና የተዘፈቀ፤ ወደ ግዳጅ ሲወጣ የሚሰጥ ገንዘብም ሆነ ከግንባሩ እንቅስቃሴ የሚገኘውን ገቢ ያለምንም ተቆጣጣሪ ወደኪሱ በማስገባት የሻቢያ የድህንነት ሰራተኞችና የሱ አቀረቦች ቢራ መጠጫ ያደረገ ምንም አይነት የቁጥጥር ስርአት የማይገዛው ሰው ነው። አበሩ ግንባሩን በማዳከም ከሚጠየቁት አንዱ ነው። አበሩ ከለልተኛ ከመሆኑም በተጨማሪ ፊደል የቆጠረ የማይወድና እንኳን ጠር ሊመራ አጀንዳ እንኳ በአግባቡ መያዝ የማይችል ሰው ነው። በ1996 ሚያዚያ ከወልቃይት የወያኔ ንብረት ነው በሚል 570 ከብቶችንና አራት ግመሎች ያዘረፈና ለሻቢያ ያስረከበ ነው። ለማስመሰል ሲሉ ግን ሻቢያና አበሩ ከብቶቹን ከተረከቡ በኋላ ድራማ ሰሩ። ጠሩ በራሱ ዘርፎ እንደመጣ አስመስለው አስወሩ። ከብቶቹን ያመጣው የወልቃይት ግንባር መሪና ለማ ግን በአበሩ ታዞ እንዳመጣ አስረድቷል። ሻቢያና አበሩ ሌላውን የአበሩን ተቀናቃኝ ለማም በዚህ ሰበብ ታስሮ ወደ እስር ቤት ተላከ። ለማም ከእስር አምልጠ የት እንደገባ አይታወቅም። አበሩ ከሻቢያ በተሰጠው ትእዛዝም እነዚህ ንብረቶች በጦርነቱ ወቅት የወያኔ ጦር ከኤርትራ የተዘረፉ ናቸው በሚል ሽፋን ለአከባቢው ገበሬዎች የኔ ከብቶች ናችሁ ብላሁ ውሰዱ ብሎ ያስወሰደ እና የኢሕአግን ሰራዊት የህዝባቸውን ንበረት ዝረፉ ብሎ ያዘዘ ነው። በነተሰፋየ ጊዜ ለጠሩ ይሰጠው የነበረው ትእዛዝ እንኳን ከብትን የሚያክል ነገር የሚበላ እንኳ «ምን ቢርባችሁ ባለቤቱ ካልፈቀደላችሁ አንዲት ጥሬ እንኳ እንዳትነኩ» የሚል ጥብቅ ማስጠንቀቂያ ነበር። አበሩ አታላይ/መስከረም ዛሬ በኢሕአግ በወንጀል የሚፈልግ እንጅ እሱ እንደሚለው እንደመሪ የሚቀበለው የለም። ሙሴና አበሩ በሻቢያ ትእዛዝ ሌላ ተለጣፊ ኢሕአግ ይመሰርቱ ካልሆነ ለኢትዮጵያ ሉአላዊነት የቆመውን ኢሕአግን የመወከል ሞራላዊ ብቃት የላቸውም።

---

ክፍል ሁለት

## ከኢትዮጵያ ጠላቶች የሚገኝ ስጦታ የለም !!

በዚህ ክፍል

«የኢሕአግ ጦር ጋር ግንኙነት አለን እየረዳነው ነው» በሚል በስሙ ስለሚነግዱት ግን ቤሳ ቤስቲን ለታጋዩ አድርሰው ስለማያውቁት ግለሰቦችና ሌሎች ሃይሎች ትንሽ እንላለን።

………..

እስከዚያው የኢህአግን ትግል ማገዝ ለሚፈልጉ የምናሳስበው ነገር ቢኖር እርዳታቸው በትክክል በትግሉ ሜዳ ላይ ላሉት አርበኞች መድረሱን፤ የተረፋትን የኢሕአግ ታጋዮች በሻቢያና በቅጥረኞቹ ለማጥፋት አለመዋሉን የማረጋገጥ ሃላፊነት እንዳለባቸው በጽኑ ለማስገንዘብ እንወዳለን።

ይቀጥላል……

ግልባጭ፦

1. በኢትዮጵያ አንድነት ለሚታገሉ ግለሰቦችና ድርጅቶች
2. ለኢትዮጵያውያን ድረ ገጾች
3. ለነጻው ፐሬስ
4. ለኢትዮጵያውያን ኢሜል የውይይት መረኮች